ሊሆን የሚገባውን ሕግ ወስናችሁ ስጡኝ አሏቸው ፤ እነርሱም የንጉሡን ቀና አስተያየት የሃይማኖቱን ፍጹምነት የሐሳቡን ቅዱስነት ተመልክተው ወዲያውኑ ተሰብስበው አሁን ፈውስ መንፈሳዊ እየተባለ የሚጠራውን ሕግ ወስነው አቀረቡለት ይባላል ። ይኸም ሕግ ፍጹም መንፈሳዊ አመራርን ብቻ በተለይም ድርቅናን ያዘለ ሕግ እንጅ አህጉራዊ ፍትሕን የማይመለከት በመሆኑ ምኞቱ ያልተፈጸመለት መሆኑን በየጊዜው ይገልጥ እንደነበር ከኢትዮጵያውያን አልፎ ለግብፃዊው ጴጥሮስ አብደል ሰይድ እንደገለጠለት እንረዳለን ። እርሱም ይህ ፍትሐ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ በዓረብኛ እንደሚገኝና ቢተረጎም ጠቃሚ መሆኑን ምኞቱም እንደሚፈጸምለት ገልጦ ነገረው ፤ እንግዲያውስ ከማንኛውም ሰው ይልቅ አንተው ፪ቱንም ዓይነት ቋንቋዎች ታውቃለህና ፈጽምልኝ ብሎ ስለጠየቀው ከዓረብ ወደ ግዕዝ ፍትሐ ነገሥትን ተርጉሞ እንደሰጠው በመቅድሙ ሊቃውንቶቻችን ያብራራሉ ። እንግዲህ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በመጀመሪያ ሊቃውንቱን እንደ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ብሔራዊ ሕግ እንዲሠሩለት ስለጠየቀ ፤ ቀጥሎም የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ውሳኔ በሀገሩ ቋንቋ ተተርጉሞ እንዲሠራበትና መንፈሳዊ አስተዳደር እንዲኖረው በመጣሩ የሕግ ሰው መሆኑን በግልጥ ለማስታወቅ ዘርዓ ያዕቆብን ቆስጠንጢኖስ ብለው ሰይመውታል ፤ ስለዚህም ዘተሰምየ ቆስጠንጢኖስ ተብሏል ።

በፍትሐ ነገሥቱ ላይ ከአበው ውሳኔ ጋር ግብፃውያን በተለይ ያስቀመጡት ዕዝል ቅጥል « ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሢሙ መምህራኒሆሙ » የሚል ይገኛል ፤ ይኸም ከግል ፍላጐታቸው የተነሣ የደቀሉት ነው ። እርሱም ሥርዋጽ በሚለው ትእምርተ ጥቅስ እንጅ በተለመደው አጠቃቀስ በአንቀጽ ውስጥ የገባ አይደለም ። በዚህም መልክ ሥርዋፅ እያለ በየአንቀጹ መካከል የሚገባ ብዙ አለ ፤ እርሱንም በጥብቅ ሲመረምሩት አብርሃም ቀሲስ በራሱ ፈቃድ ያስገባው ይመስላል ፤ ትርጉሙም ሥርዋጽ ማለት « የጠመመ ማቅኛ የጐደለ መሙሊያ » ነው ይላሉ ፤ ስለዚህም ያልተቃና ሐሳብ ባለበት ሁሉ የራሱን ፍላጐት ለማሟላት ሲል በየቦታው አስገብቶበታል ለማለት ይቻላል ። ይኸም ዕንቅፋት የሆነ አንቀጽና ሌላም ይኸን የመሰለ አስቸጋሪ አንቀጽ እያለ በኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት ቅዱስ ሕግ ፤ እየተባለ ሲከበር ይኖራል ። በቤተ ክርስቲያናችን አሁንም ቢሆን ሌላ ሕግ የለም ገናም አልወጣም ሆነም ቀረ የሚጠቀሰው ፍትሐ ነገሥቱ ብቻ ነው ፤ ይኸም ማለት ክፋውንም ደጉንም እንዳዘለ ይዞ ይገኛል ማለት ነው ። በመንግሥት በኩል ግን ፍትሐ ነገሥቱ የምንጭነት ሥልጣን ሳይነፈገው በሕግ በኩል ራሱን የቻለ ሌላ ሕግ ሠርቶ እርሱን በመድበልነቱ ብቻ ይጠቀምበታል ። ፍትሐ ነገሥት በታሪክ በኩል ይኸን የመሰለ ዋጋ ሲኖረው ከላይ እንደገለጥኩት በቤተ ክርስቲያን አሁንም ገና የሕግነት ቦታውን እንደያዘ ይገኛል ፤ ይሁን እንጂ በታሪክነቱም በሕግነቱም ቢሆን ብዙ ፈላጊ አለው ፤ ስለዚህም በአንድምታ ትርጓሜ ፤ በነጠላ ትርጓሜ በእንግሊዝኛ ታትሞ ይገኛል ። ወደፊት ግን ጊዜ ቢገኝ ግዕዙን አስተካክሎ

መተርጐም ሳያስፈልግ አይቀርም ፡፡ ፍትሐ ነገሥቱ በሕግነት መልክ ባይሠራበትም ቅሉ ሁሉም ፍትሐ ነገሥት እንዲህ ይላል የሚለውን ጥቅስ ለመስማት ይጓጓል ፤ ስለዚህ መጽሐፉን ለማንበብ ታሪኩን ለመስማት ምሥጢሩን ለመረዳት የሚፈልገው ብዙ ነው ፡፡

## ልዩ አስተያየት ፡፡

፩/ በኢትዮጵያ የሕግ መጻሕፍት ብዙ መሆናቸውን ለመግለጥ ያህል ስማቸውን ሁኔታቸውን በመግለጥ ጻፍን እንጂ ፡፡—

ሀ/ አደባባይ ወጥቶ የሚታወቀው ፤

ለ/ በጉባኤ የሚኬደው (የሚተረጐም) ፍትሐ ነገሥቱ ብቻ ነው ፡፡

፪/ ሌሎች የሕግ መጻሕፍት የሕግ መጻሕፍትነታቸው በፍትሐ ነገሥቱ ስለተገለጠ የኛ ቤተ ክርስቲያን ቀርታ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በሕግ መጽሐፍ ሊስት ላይ ያስቀምጧቸዋል ፤ በኛ ግን የዓይን አንድም የንባብ መጽሐፍ ዋጋ የሚሰጣቸው ይመስላል ፡፡

፫/ ሁሉም ታትመው አንድም ተባዝተው በየእጁ ለሁሉ ስላልተዳረሱ የብዙዎች መጻሕፍት ስማቸው እንጂ ዝርዝር ነገራቸው ሙሉ አንቀጻቸው አይደለም ፡፡